# ጋዜጣዊ መግለጫ

ግንቦት 23 ቀን 2015 ዓ.ም

## በደቡብ ኢትዮጵያ የተለያዩ ክልሎች የሚካሄድ ሀገራዊ የሽግግር ፍትህ የህዝብ ምክክርና ግብአት የማሰባሰብ ስራ መርሀ-ግብር ስለመጀመር

በአገራችን ሲስተዋሉ ከቆዩ መጠነ-ሰፊ እና ውስብስብ በደሎች፣ ፈተናዎች፣ ግጭቶች እና ከባድ የሙብት ጥሰቶች በመነሳት - ሙሉ ፍትህ የሚሰጥበትን መንገድ ለመዘርጋት እና ማህበረሰቡ ወደቀደመ ሁኔታው እንዳይመለስ ለማድረግ የሚያስችል ዘላቂ ሰላም፣ እርቅ እና የህግ የበላይነት የሰፈነበት ሥርዓት መገንባት ፍፁም አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል።

የሽግግር ፍትህ ስርአትን ተግባራዊ ማድረግ ለአገራችን ዘላቂ ሠላም፣ ዲሞክራሲ እና ዕድገት ጉልህ ሚና የሚጫወት መሆኑን በመገንዘብ የኢትዮጵያ መንግስት ሂደቱን በተሟላና በተቀናጀ መልኩ ለመተግበር የሚያስችሉ የተለያዩ ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል።

በዚህ ረገድ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማርቀቅ ስራ ለመጀመር የሚያስችለው 'የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች' መነሻ ሰነድ የፍትህ ሚኒስቴር ባደራጀው ከፍተኛ የባለሙያዎች ቡድን ተጠናቋል። ለሀገራዊ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት የሚያስፈልገው ብሄራዊ ምክክር የማስጀመሪያ ስነ-ስርአት ሰኞ የካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም (March 6, 2023) ሚኒስትሮች፣ የክልል ርእሰ-መስተዳድሮች፣ የፌዴራል እና የክልል ፖሊስ ኮሚሽነሮች እና የፀጥታ ዘርፍ ሀላፊዎች፣ የፍርድ ቤቶች እና ፍትህ ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች፣ ታዋቂ ግለሰቦች እና አግባብነት ያላቸው የተመድ ኢትዮጵያ ጽህፈት ቤት ሀላፊዎች በተገኙበት በደማቅ ሁኔታ መከናወኑ ይታወሳል።

ይህን ተከትሎ በክልሎች ደረጃ የሚካሄደው ምክክር በመላው አገሪቱ በሚገኙ ከሀምሳ ስምንት በላይ ከተሞች ከሚያዝያ እስከ ነሃሴ 2015 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ለማከናወን መርሀ-ግብር ወጥቷል። በዚህ አግባብ የህዝብ ምክክሩ የመጀመሪያው ምእራፍ በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ከተሞች በስኬት የተከናወነ ሲሆን - ሁለተኛው ምእራፍ ከዛሬ ግንቦት 23 ጀምሮ እስከ ሰኔ 10 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ በሲዳማ ብሄራዊ ክልል፣ በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ብሄራዊ ክልል፣ እና በደቡብ ብ/ብ/ህ ብሄራዊ ክልል በተመረጡ አስራ ሁለት የተለያዩ ከተሞች ይካሄዳል።

ለምክክሮቹ - ፍጹም ነፃ እና ገለልተኛ በሆነ ሂደት የሚለዩ እና የሚጋበዙ፣ ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎች የሚወክሉ ግለሰቦች እና ባለድርሻ አካላት የሚጋበዙ ይሆናል። ተሳታፊዎችም በባለሙያዎች በሚቀርቡ አማራጭ የፖሊሲ ሀሳቦች ላይ ክርክር በማካሄድ በነፃነት የፖሊሲ አማራጭ ሰነዱን ለማዳበር የሚያስችሉ ግብዓቶችን እንዲያጋሩ ይጠበቃል።

**የሽግግር ፍትህ ከፍተኛ የባለሙያዎች ቡድን**

**ፍትህ ሚኒስቴር**